# <u>በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱአምላክ አሜን</u>

*በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በትምሕርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ዋና ክፍል የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ፕሮግራም ከ**መስከረም** □**እስ**ከ ነሐሴ **2003** ዓ.**ም** የተሰሩ ስራዎች፡፡*

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባር ወንጌለ መንግሥት ለዓለም ማዳረስ ነው፡፡ በዚህም ላለፉት **2000** ዓመታት ያህል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወንጌለ ክርስቶስን በየዘመኑ በተለያዩ መንገዶች ስታስፋፋ ቆይታለች፡፡ ይሁን እንጂ ዘመን ዘመናትን ሲያስቆጥር የስብከተ ወንጌሉ አገልግሎት የምዕመናንን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ፤ ጊዜው የሚጠይቅውን አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለበት ደረጃ ደርሷል፡፡ ቤተ ክርስቲያን በዚህ አገልግሎት ለሌሎች አህጉር መድረስ የሚገባት ቢሆንም ቅሉ ለሀገረ ውስጥ ምዕመናን እንኳ ሙሉ በሙሉ ወንጌልን ማድረስ አልቻለችም፡፡ በስብከተ ወንጌል አገልግሎት የተሰማሩ አገልጋዮች ወይም ደቀመዛሙርት ቁጥር ከምዕመናን ፍላጐት አንጻር የሚመጣጠን አይደለም፡፡ በሀገራችን በ**1999**/ **2000** ዓ.ም**.** በተደረገው ሀገር አቀፍ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች አኃዛዊ ቁጥር የጨመረ ቢሆንም የሌሎች «እምነቶች**ን**» በንጽጽር ቤተክርስቲያን ያላት ድርሻ በመቶኛ ካለፉት ጊዜያት ጋር ሲነፃፀር እየቀነሰ በመምጣቱ እና በገጠርና ጠረፋማ አካባቢዎች ያሉ ምዕመናን የሚያስተምራቸውና በሃይማኖት የሚያጸናቸው የወንጌል መምህር ፍላጐት አንጻር እየተሰጣቸው ያለው ምላሽ በጣም ዝቅተኛ መሆን የጉዳዩን አሳሳቢነት ያሳያል፡፡

የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን ሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ቅዱስ ሲኖዶስ የሰጠውን ሓላፊነት ለመወጣት ባለፉት **19** /አስራ ዘጠኝ/ ዓመታት በተለያዩ መንገዶች ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፤ እያደረገም ይገኛል፡፡ ሆኖም ግን ሁሉንም የቤተክርስቲያን አባላት ባሳተፈ እና እያንዳንዱ ምዕመን የድርሻቸውን እንዲወጡ በማድረግ ችግሩን ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ፤ ስብከተ ወንጌል አገልግሎት ባልተስፋፋባቸው ገጠርና ጠረፋማ ቦታዎች፤ አኅዛብና መናፍቃን በበዛባቸው አካከባቢዎች ወንጌልን ለማዳረስ የአሥር ዓመት የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ማስፋፊያ ኘሮግራም በመቅረጽ በግንቦት **19**/**2002** ዓ.ም**.** አገልግሎቱን ጀምሯል፡፡

ኘሮግራሙ በተመረጡ ሃያ/20/ ሀገረ ስብከቶች፣ መቶ/100/ ወረዳ ቤተክህነቶች እና ከአንድ ሺህ/1000/ በላይ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ተግባራዊ የሚሆን ሲሆን፤ የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ በተያዘለት አሥር/10/ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሃያው/20/ ሀገረ ስብከቶች፣ በአምስት/5/ የተለያዩ መንገዶች የስብከተ ወንጌል አገልግሎት መስጠት እና በሃያው/20/ ሀገር ስብከት እና በሥራቸው በሚገኙ ወረዳ ቤተክህነቶች የአቅም ማጐልበቻ ሥራ በመሥራት ስብከተ ወንጌልን በራሳቸው እንዲያስፋፉ ማስቻል ነው፡፡

በመሆኑም ሃያው/20/ ሀገረ ስብከቶች በስብከተ ወንጌል አገልግሎት እስከ አሁን ድረስ ያለባቸው ችግሮች፤ የሌሎች እምነቶች መስፋፋትና ተጽእኖ እስከምን ድረስ እንደሆነ፤ ስብከተ ወንጌል ለማስፋፋት ያላቸው ሀብት ምን እንደሆነ፤ ለእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት በምን መንገድ ስብከተ ወንጌል ማስፋፊያው ሥራውን ቢሠራ ውጤታማ እንደሚሆን የሚያሳውቁ ዝርዝር መረጃዎች ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህ መረጃዎች ለማግኘት ፕሮግራሙ የሚተገበርባቸው ሀገረ ስብከቶች ነባራዊ ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችል የቅድመ ትግበራ ጥናት **(**Base line servay**)** ሥራ ተሰርቷል፡፡የዚህም ሥራ ውጤት በመጋቢት **11**/**2003**ዓ.ም በኢትዮጲያ ስብሰባ ማዕከል የፕሮግራሙ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የ**14**ቱ አ/ስብከቶች የቅድመ ትግበራ ጥናት መገልጹ ይታወሳል፡፡

በአጠቃላይ ፕሮግራሙ ይፋ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን የፈጸማቸውን ዋና ዋና የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ አገልግሎቶች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

1. **የሕዝብ ጉባኤያትን ማዘጋጀት፡-** በዚህ ዓመት □እንዲካሄዱ ከታሰቡት ከሃያው/20/ ሀገረ ስብከት መቀመጫ ከተሞች የሕዝብ ጉባኤያት አስራ ስድስቱ/16/ ማለትም **በጅማ ሀ/ስብከት-** ጅማ ከተማ፣ **ጋሞ ጎፋ ሀ/ስብከት** በአርባ ምንጭ ከተማ ፣ **አፋር ሀ/ስብከት**-አዋሽ ሰባት ከተማ፣ **ሐዲያና ስልጤ ሀ/ስብከት-** ሆሳዕና ከተማ ፣ **ድሬደዋ ሀ/ስብከት-** ድሬደዋ ከተማ፣ **አጋዴን እና ሶማሌ ሀ/ስብከት** -ጅጅጋ ከተማ ፣ **ከንባታ አላባና ጠንባሮ ሀ/ስብከት-** ዱራሜ ከተማ፣ **ምስራቅ ሐረርጌ ሀ/ስብከት** - ሐረር ከተማ፣ **ሸካ ቤንች ማጂ ሀ/ስብከት** - ሚዛን ተፈሪ ከተማ ፣**ከፋ ሀ/ስብከት** - ቦንጋ ከተማ እና **ደቡብ ኦሞ ሀ/ስብከት** - ጂንካ ከተማ የሕዝብ ጉባኤያት ተደርገዋል፡፡ በዚህም አገልግሎት የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀመዛሙርት፣ የሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀመዛሙርት፣ የማኅበሩ መምህራን እና የግል ዘማሪያን የተሳተፉባቸው ሲሆን በአጠቃላይ ሰባ ሰባት ሺህ ብር /**77.000.00**/ወጭ ተደርጎባቸዋል፡፡**ከነዚህ በተጨማሪ አምስቱ/5/ ማለትም አሶሳ ሀ/ስብከት** -አሶሳ ከተማ ፣ **ኢሉ አባቡራ ሀ/ስብከት -** መቱ ከተማ ፣ **ምዕራብ ወለጋ ሀ/ስብከት-** ጊምቢ ከተማ፣ **ምዕራብ ሐረርጌ ሀ/ስብከት** - አሰበ ተፈሪ ከተማ፣ **ጉጂ ቦረና ሊበን ሀ/ስብከት-** ሃገረ ማርያም ከተማ በተደረጉት ሐዋርያዊ ጉዞዎች አማካኝነት ጉባኤያቱ ተካሂደዋል፡፡

2. **ሐዋርያዊ የስብከተ ወንጌል ጉዞ ማድረግ፡-** በፕሮግራሙ ስድስት ጉዞዎች የተከናወኑ ሲሆን፤ **አንደኛው፡-** በጅማ **በጅማ ሀ/ስብከት** (*በሊሙና ሰኮር ወረዳዎች*) □እና **ኢሉ አባቡራ ሀ/ስብከት** (*መቱ ከተማና ዙሪያው፣ ጎሬ -አሌ፣ ደንቢ -ደዴሳ፣ ያንፋ -ቦረቻ፣መረቦ ወረዳዎች)* ያዳረሰ ጉዞ ነበር፡፡ በዚህም ጉዞ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀመዛሙርትና የማኅበሩ መምህራን የተውጣጣ የመምህራን ቡድን፤ የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች የተውጣጣ የመዘምራን ቡድን የያዘ በጠቅላላው ሃያ ልዑካንን ያሳተፈ ሐዋርያዊ የስብከተ ወንጌል ጉዞ ተፈጽሟል፡፡ **ሁለተኛ፡-ጋሞ ጎፋ ሀ/ስብከት በ አርባ ምንጭ ዙሪያ አምስት ወረዳዎች** (*ዳራማሎ-ሳሜ፣ ጎፋ-ሳውላ ፣ ዑባ ደብረ ፀሐይ ፣ ገልማ -ዛላ ፣ ሠላም-በር* )፤ **ሦስተኛ** :-ምዕራብ ሐረርጌ ሀ/ስብከት አሰበ ተፈሪ ዙርያ አምስት ወረዳዎች (*አሰበ ተፈሪ ከተማ ፣መቻራ፣ ገለምሶ፣ በዴሳ ፣ ሂርና*)፤ **አራተኛ፡- ምዕራብ ወለጋ ሀ/ስብከት** (*መንዲ፣ ነጆ ፣ጊንቢ ወረዳዎች* ) □**እና አሶሳ ሀ/ስብከት** (*አሶሳ ማእከል፣ ባብባሲ ቆማሼ ወረዳዎች*)፤**አምስተኛ፡- ሐዲያና ስልጤ ሀ/ስብከት** አምስት ወረዳዎች (*ዳሎቻ፣ ወራቤ ፣ ምርሲሶ ፣ ሆሚቾ፣ ጊምቢቾ*) **ስድስተኛ፡- ጉጂ ቦረና ሊበን ሀ/ስብከት** ባሉ አምስት ወረዳዎች (*ሀገረማርያም፣ ያቤሎ፣ ተልተሌ ፣ ሜጋ፣ ኢዲሎላ*) ያዳረሱ ሐዋርያዊ ጉዞዎች ተከናውነዋል፡፡በነዚህም ጉዞዎች የግል ዘማሪያንና መምህራን፣የማኅበሩ መምህራን እና መዘምራን የተሳተፉባቸው ሲሆን ከዚህ በተለየ በአ/አበባ ሀ/ስብከት ካሉ ሰ/ት/ቤቶች አንዱ የሆነው የደብረ ዕንቁ ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተክርስቲያን መሠረተ ሕይወት ሰ/ት/ቤት በሊበን፣ጉጂ ቦረና ሊበን ሀ/ስብከት በተካሄደው ጉዞ የመዘምራኑን ቡድን በመላክ እና ጉዞው ከጠየቀው አርባ ሺህ ብር /**40.000**/ ላይ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ብር /**9.800**/ ያህሉን በራሱ ሸፍኖ ፕሮግራሙ የሚጠይቀውን አገልግሎት ፈጽሟል፡፡ ከነዚህ ጉዞዎች በአጠይ ከ ብር /**22**ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሺህ **5.000.00**/በላይ ወጭ ተደር□ል፡፡

3. **በራሪ ትምህርታዊ ጽሑፎች ተዘጋጅተው ተሰራጭተዋል፡-** የልደት እና የጥምቀት እንዲሁም የትንሣኤን በዓ**ላት** ምክንያት በማድረግ በሁለት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛና በኦሮምኛ ቋንቋ ሃምሳ ሺህ /**50.000**/ኮፒ በራሪ ወረቀት በ አስራ አምስት ሺህ /15.000/ብር ተዘጋጅቶ በአሥራ ስድስት ሀገረ ስብከቶች ተሰራጭቷል፡፡ በዚህ አገልግሎት ምዕመናን አፍ በፈቱበት ቋንቋቸው ቤተ ክርስቲያን የምታስተምር መሆኗን ያረጋገጡበት፣ በአንዳንድ

አካባቢዎች የትራክቱ ሥርጭት በማነሱ ምዕመናን በገንዘብ እንዲሸጥላቸው የጠየቁበት አጋጣሚዎች የታየበት አገልግሎት ነበር፡፡

4. **በተለያዩ ቋንቋዎች የስብከተ ካሴት ማዘጋጀት፡-** እስከአሁን ሁለት የአማርኛ ስብከትና ትምህርት በድምጽ፣ በድምጽ ወ ምስል እና በካሴት አምስት ሺህ ቅጂ ያሠራጨ ሲሆን፡ አንድ የኦሮምኛ ትምህርት በድምጽ እና በካሴት **3ሺ.ህ ቅ**ጂ ለስርጪት ዝግጁ ያደረገ ሲሆን በወላይተኛ ቋንቋ አንድ የመዝሙር ካሴት **1200**/አስራ ሁለት ሺህ/ ቅጂ አሰራጭቷል፡፡ በተጨሪም በሲዳምኛ ቋንቋ ስብከት እየተዘጋጀ ሲሆን ለእነዚህ ስራዎች ወደ አንድ መቶ አስራ አምስት ሺህ /**115.000**/ ብር ያህል ወጭ ተደርጎባቸዋል፡፡

5. በፈንታሌ ወረዳ በጡጢ ቀበሌ የሚገኙ የከረዮ ጐሣ አባላት /ቦሰና ዱላቻ/ የተባሉ ቁጥራቸው ወደ **114** የሚሆኑ አባዎራዎች ለፕሮግራሙ እንዲያስተምር በቀረበለት ጥሪ መሰረት አስተምሮ እንዲጠመቁ አድርጓል፡፡

6. በየተለያዩ ባለድርሻ አካላት ፕሮግራሙ በግልጽ በተለይ ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ከወረዳ ቤተክህነት ሊቃነ ካህናት ጋር እና ሰንበት ት/ቤቶች ተወካዮች ጋር በተመረጡት ሀገረ ስብከቶች በጋራ ስለሚፈጽሟቸው አገልግሎቶች ውል ተፈራርመዋል፡፡

7. በከንባታ እና አላባ ጠንባሮ ሀገረ ስብከት አንድ የስብከተ ወንጌል መምህር በመቅጠር የአካባቢውን ምዕመናን ወንጌልን በአግባቡ እንዲማሩ እያደረገ ይገኛል፡፡ የዚህን መምህር ወርኃዊ ደመወዝ በአንዲት በጐ አድራጊ ምዕመን የተሸፈነ ነው፡፡ከነዚህ ተተኪ መምህራን ሁለቱ በተልተሌ ወረዳ ወደ **200** የሚሆኑ ሰዎችን በኦሮምኛና በኮንሶኛ ቀንቀ አስተምረው በማሳመን ጥምቀት እንዲፈጸምላቸህው ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

8. ከነገሌ ቦረና ሀገረ ስብከት ለመጡ **4** ተተኪ መምህራን የስብከተ ወንጌል ስልጠና እንዲያገኙ በማስቻል ለመጡ በት ወረዳ ምዕመናን በቋንቋቸው እንዲያስተምሩ በማሰማራት እየተከታተለ ይገኛል፡፡

9. ምዕመናን ባሉበት ሆነው ለዚህ ፕሮግራም ድጋፍ በማድረግ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ለማድረግ በተለያዩ ሀገረ ስብከቶች በማኅበሩ መዋቅር ሥር ባሉ ማዕከላት አማካኝነት ፕሮግራሙ ን አስተዋውቀዋል በማስተዋወቅም ላይ ይገኛል፡፡

10. ጥያቄ መላሽ የሆነ መድብል በአማርኛ ተጽፎ ህትመት ላይ ሲሆን ፤ በኦሮምኛ እንዲሁ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በፕሮግራሙ ከተተገበሩ በርካታ አገልግሎቶች መሀል አንኳር አንኳሮቹ ከላይ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ቀጣይ አገልግሎቶቹ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማስቻል በእግዚአብሔር ቸርነትም የአገልግሎቱን ፍሬ በተጨባጭ ለማየት እንዲያስችል የመሠረታዊ የቅድመ ትግበራ ጥናት (Base line survey) ከፍተኛውን የጊዜና የሰው ሐይል የጠየቀ ሥራ ነበር፡፡ ከዚህም በመነሣት ቀጣዮን አገልግሎት በቸርነቱ እንድንፈጽም እግዚአብሔር ይርዳን አሜን፡፡

***በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን***

***በትምሕርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ዋና ክፍል የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ፕሮግራም***

"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው..." ማቴ ፳፰፥፲፱

በደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ከሚገኙ ወረዳዎች በሴኔጋልእና ቶልታ ወረዳዎች የተደረገ ስርዓተ ጥምቀት በከፊል





የቶልታ ወረዳ ምእመናን በከፊል





የሴኔጋል ወረዳ ምእመናን በከፊል



